# ትምህርት አንድ ድነት (መዳን)

## ሀ፡ የእግዚአብሔር ዕቅድ (የንባብ ክፍል፡ ዘፍ.1-2)



ማንም ሰው ከእግዚአብሔር አምላክ ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖረው የእርሱንም መንግስት ለመውረስና ከእርሱም ጋረ ለዘላለም ለመኖር ይመኛል። እግዚአብሔር አምላክ በመጀመሪያ ሰውን ሲፈጥረውም በዕቅድና በዓላማ ነበር። ዓላማውንም እግዚአብሔር አስቀድሞ የፈጠራቸውን ነገሮች ሁሉ እንዲገዛና ከእግዚአብሔርም ጋር ኅብረት ኖሮት ለዘላለም እንዲኖር ነበር።

የሰው አፈጣጣር ከሌሎቹ ሁሉ የተለየ ነበር። ሌሎቹ በቃል ሲፈጠሩ ሰው ግን በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ፣ ከአምላክ ጋር ህብረት ለማድረግ እንዲችል መንፈስ ያለው መሆኑ፣ የሚያስብና የሚያስተውል አዕምሮ ያለው መሆኑ፣ ክፉውን ከመልካሙ በመለየት በወደደው መንገድ ለመሄድ የሚያስችል ፈቃድና ህሊና ያለው መሆኑን ያጠቃልላል።

አዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ በእነዚህ መልካም ነገሮች ብቻ የተሞሉ አልነበሩም። በውጪና በዙሪያቸው ከሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ ምንም ያልጎደላቸው ነበሩ። አየር ህልውና አብሯቸው ነበር። እግዚአብሔር አብሯቸው ከኖረ ኑሯቸው ሙሉ ነው ማለት ነው። ዕረፍት፣ ሰላም፣ ደስታ፣ የዘላለምም ህይወት አላቸው። ይህን ህብረት እስከጠበቁ ድረስ ደግም ክፉ ነገር አያገኛቸውም ሞትንም አይሞቱም።

## ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ዕቅድ ምን ነበር?

2. የሰውን አፈጣጠር ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?

3. ሰው በአምሳለ አምላክ ተፈጠረ ሲባል ምን ማለት ነው?

4. ሰው ከአምላክ ጋር ህብረት ሲኖረው ውጤቱ ምንድን ነው?

## ለ፡ የሰው ውድቀት



እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሰጠው ስጦታ አንዱ የምርጫ ነጻነት ሲሆን ይህን ያደረገው ሰው ያለግዴታ በፈቃደኝነት እንዲታዘዘውና እንዲከተለው ሲል ነው። ይህን ፈቃደኝነቱን ለማረጋገጥም በዔደን የአትክልት ስፍራ እንዳይበሉ የተከለከሉት ዛፍ ነበር (ዘፍ.2፡9)። አዳምና ሔዋን ፈቃድ ቢኖራቸውም ኃጢአትን ላለመስራት ችሎታም ነበራቸው። እግዚአብሔር መታዘዛችን ከፈቃዳችን እንዲመነጭ ይሻል። እርሱ የሚወደው በምርጫችን ስንገዛለት ነው።

ሰይጣን በተንኮሉ ሔዋንን በማሳት ሰውን ሁሉ በደለኛና ዓመጸኛ አደረገው። አዳም እንዳይበላ የታዘዘውን ዛፍ ፍሬ በመብላት ሰይጣንን መታዘዝን ወይም እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ መረጠ። ባለመታዘዙም ኃጢአትን ሰራ፤ አስቀድሞም የተመደበውን ፍርድ ተቀበለ። ፍርዱም ሞት ነበር። (ዘፍ.2፡16-17) ይህ ሞት ስጋዊ ሞት ሳይሆን መንፈሳዊ ሞት ነበር። ይህም ከአምላክ መለየት ነበር፤ ይሁን እንጂ ስጋዊ ሞትም የዚህ ፍርድ አንድ ቅርንጫፍ ነው። የሰው ዘር ሁሉ ምንጭ የሆነው አዳም በኃጢአት በመውደቁ ሰው ሁሉ በኃጢአት አዘቅት ውስጥ ወደቀ። (ሮሜ.5፡12)

ኃጢአት ሰውን ከአምላኩ፣ ከሌላ ሰው ፣ከራሱ እንዲሁም ከተፈጥሮም ጋር ሳይቀር አጣላ። በተለይም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የጥልን ግድግዳ አኖረ። የሰውንም ዘር ሁሉ ከማህጸንም ጀምሮ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር የተለየ እንዲሆን አደረገ። (መዝ.51፡5) አዳምን ሔዋን የሰይጣንን አሳብ ከሰሙና ከታዘዙ፤ በኃጢአትም ከወደቁ በኋላ ከ እግዚአብሔር ፊት ተደበቁ። ድምጹን ሲሰሙ ይደነግጡ ፊቱንም ሊያዩ ይፈሩ ጀመር። ስለዚህም ከፊቱ በርግገው በጫካ መደበቅን መረጡ። ይህ ነገር በእነርሱ ብቻ ሳያበቃ ዛሬም ሰው ሁሉ በደለኛ በመሆን ከኃጢአት በታች ወድቆ፣ ከእግዚአብሔርሔር ክብር ጎድሎ፣ ፍርደኛ በመሆን ከአምላኩ እየሸሸ እንዲኖር አድርጎታል። (ሮሜ.3፡23) በአንዱም በአዳም ኃጢአት ሁላችን ኃጢአተኞች ሆንን ሁላችንም ሞትን።፡( 1ቆሮ.15፡22)

ዛሬ የምናያቸውና የምንሰማቸው እጅግ የበዙ መጥፎ ድርጊቶችና ነገሮች አሉ። እነዚህ ነገሮች በራሳቸው ኃጢአት ናቸው። ከዚህ በላይ ግን እነዚህ ነገሮች የዋናው ኃጢአት ማለትም እግዚአብሔርን የመሸሽ ቅርንጫፍና ውጤቶች ናቸው። እውነተኛ መፍትሔ ለማግኘት መደረግ ያለበት ቅርንጫፎችን መመልመል ሳይሆን ስርን መንቀል ነው።

ጥያቄዎች፡

1. ሰው ለእግዚአብሔር እንዲታዘዝ የተዘጋጀው መፈተኛ ምን ነበር? ለምንስ ተዘጋጀ?

2. አዳምና ሔዋን ላለመታዘዝ ይችሉ ነበር? ያለመታዘዛቸውስ ፍርድ ምን ነበር? ውጤቱስ?

3. የአዳምና የሔዋን መተላለፍ በሰው ዘር ላይ ያመጣው መዘዝ ምንድን ነው?

## ሐ፡ የሰው ሙከራ



ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ከተጣላና ከተለያየ በኋላ ከእርሱ ጋር ለመታረቅ እስከ ዛሬ ድረስ በብዙ መንገድ ሞክሯል። ሰው ሲፈጠር ከአምላኩ ጋር ኅብረት በማድረግ ሳይለያይ ለመኖር ነበርና የተፈጠረው ይህ እስካልሆነ ድረስ ነፍሱ ዕረፍትን አታገኝም። በእርሱና በአምላኩ መካከል የተፈጠረውን የኃጢአት ገደል ሞልቶ ሊያሻግረው የሚችል ድልድይ ከማበጀት ታክቶ አያውቅም።



ህግን በመጠበቅና ለማድረግ በመታገል ተሞክሯል፣ ጨዋና በጎ አድራጊ በመሆን እግዚአብሔር ሊደረስ ተሞክሯል፣ የተለያዩ ኃይማኖቶችን በመከተል ሊደረስ ተሞክራል፣ የተለያዩ ትምህርቶችንና ፍልስፍናዎችን በመከተል ለመታረቅ ተሞክሯል፣ ራስን በመጉዳት የኃጢአትን ዋጋ በመክፈል ለመታረቅ ተሞክሯል፣ ሌሎችም ተደርገዋል።



ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ ሰው ሰራሽ ድልድዮች ወደ እግዚአብሔር ማድረስ የሚችል ባህርይም አቅምም ያላቸው አይደሉም።

ጥያቄዎች፡



1. ከእግዚአብሔር የተለየ ሰው ዕረፍት የሌለው ለምንድነው?

2. ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ እስከዛሬ ድረስ ምን ምን መንገዶች ሞክረዋል?

## መ፡ የእግዚአብሔር መፍትሔ

### ፲. በብሉይ ኪዳን



ሰው በኃጢአቱ ይውደቅ እንጂ እግዚአብሔር ግን ጥሎ አልተወዉም። ከውድቀቱ ሊያነሳውና ከኃጢአቱም ሊያነጻው መድኃኒት እንዳዘጋጀለት ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን። አዳምና ሔዋን ከተላለፉና ከተሸሸጉ በኋላ እግዚአብሔር ወደተሸሸጉበት መጣ። እግዚአብሔር ፍጹም ጻድቅ አምላክ ነውና ፍርዱንም መፈጸም ነበረበትና እርምጃው ወዲያውኑ ተወሰደ። አሳቹ ተረገመ፣ አዳምና ሔዋን ከአምላክ ተለይተው ከኤደን ገነት ተባረሩ፤ እንዳይገቡም ተደረጉ። እግዚአብሔር ሊቀጣቸው ብቻ ሲችል ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ግን የተስፋ ቃልን ሰጣቸው። (ዘፍ.3፡15) ሌላው ያደረገላቸው ነገር ዘላቂ ልብስን ማልበሱ ነው። አዳምና ሔዋን ዕርቃናቸውን በቅጠል ሊሸፍኑ ሞከሩ። ይህ በራስ እጅ የራስን ኃጢአት መሸፈን እንደማይቻል ያሳያል። እነርሱን የቁርበት ልብስ ለማልበስ አስቀድሞ የታረደ እንስሳ መኖሩንና ደም መፍሰሱን ያመለክታል።

ኃጢአት የነፍስ ዋጋ መጠየቅ የጀመረው ከአዳምና ከሔዋን ጊዜ ሲሆን መታረቅም የደም ዋጋ መጠየቅ የጀመረው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው። ከዚህ ጊዜ አንስቶ የመጨረሻውና ኃጢአት የሌለበት የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ጸም መስዋዕት ለማቅረብ ተገደዱ። ደም ሳይፈስ ስርየት ሊገኝ አልተቻለም። ከዚህ ጊዜም ብዙ ቆይቶ የተሰጠው የሙሴ ሕግ ለኃጢአት ስርየት የነፍስን መስዋዕትና የደምን መፍሰስ ጠይቋል። (ዘፍ.4፡4፤ 8፡20፤ ዘሌ.17፡11፤ ዕብ.9፡22)

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርና ሰዎች ኅብረት ይኖራቸው ዘንድ የተሰጣቸው የሙሴ ህግ ነበር። ይህን ካፈረሱ የደም መስዋዕት ማቅረብ ነበረባቸው። በዚህም የኃጢአትን ጊዜያዊ ስርየት ያገኙ ነበር። ይህ የመታረቂያ መንገድ እግዚአብሔር ለጊዜው ያዘጋጀው እንጂ ሰዎች ወደ እርሱ እንዲቀርቡ የተሰራው ዘላቂው መንገድ አልነበረም።



**ጥያቄዎች፡**

1. ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ምን ሆነ? እግዚአብሔርስ ምን አደረገ?

2. በብሉይ ኪዳን ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቁበት የነበረው መንገድ ምን ነበር?

3. ለኃጢአት ስርየት ደም መፍሰስ ማስፈለጉ የኃጢአትን ክብደት ምን ያህል ያመለክታል?

መ፡ የእግዚአብሔር መፍትሔ (የንባብ ክፍል 1ዮሐ.5፡6-21)

2. በአዲስ ኪዳን

## እግዚአብሔር (ይቅርታ – ምህረት - ሕይወት




## ሰው (ኃጢአት – ፍርድ – ሞት

በብሉይ ኪዳን የተገለጠው የደኅንነት መንገድ በአዲስ ኪዳን ወደተገለጠው ዘላቂው መንገድ እንደሚያመራ ያለ መጋቢ መንገድ ነው። ሕግ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ነው። (ገላ.4፡24) እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን የአዳኝ ተስፋ ሰጥቶ ነበር። ይህም አዳኝ ከሴት የተወለደው ደግሞም ከሕግ በታች የተወለደው፣ ሥጋ የለበሰው አምላክ፣ የሰውን ኃጢአት ተሸክሞ በመስቀል ላይ የሞተው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (ገላ.4፡4-5)



በስጋ የተገለጠው ይህ ኢየሱስ ንጹህ ደሙን በማፍሰስ የዓለምን ኃጢአት ያስወገደው የእግዚአብሔር በግ ነው። ይህን ተስፋ ነበር እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን የሰጠውና በአዲስ ኪዳን የገለጠው። ኢየሱስ ክርስቶስ የደኅንነት ብቸኛና እውነተኛ መንገድ ነው (ዮሐ.14፡6)። በብዙ ኃይማኖቶች እንደምናየው ሰዎች በራሳቸው ጥረትና መፍጨርጨር እግዚአብሔርን ሊያገኙ ሲሞክሩ ነው። ሰዎች በራሳቸው ጥረትና መፍጨርጨር እግዚአብሔርን ሊያገኙ ሲሞክሩ ነው። ለምሳሌ በሚከተሉት መንገድ፡-

- ሰውነታቸውን በመጉዳት
- ዓለምን ከዶ በመመነንና በብትህና በመኖር

- በጎ ስራን ተግቶ በመስራት
- የተወሰኑ ሕግጋትንና ድንጋጌዎችን በመጠበቅ
- የአንድ የእምነት ድርጅት አባል በመሆንና በመሳተፍ

ሌሎችንም ብዙ ብዙ ነገሮችን በማድረግ አንድ ቀን ሲሞቱ የእግዚአብሔር መንግስት ወራሾች ለመሆን ይለፋሉ። ኃጢአተኛ ሰው በጥረቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን፣ ከእርሱም ጋር ኅብረትን መፍጠርና መንግስቱንም መውረስ አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ግን ኃጢአት ወደ ሰው ታሪክ ከገባ በኋላ ሰው ከፈጣሪው የሚሸሽና እግዚአብሔር ደግሞ ከነአዳምም ጀምሮ ኃጢአተኞችን ፍለጋ የሚመጣ አምላክ መሆኑን ነው። ማንም ሰው በኃጢአተኛው ተፈጥሮ እግዚአብሔርን የማይፈልግ መሆኑን በሮሜ.3፡11 ላይ ተጽፏል። በሉቃስ 19፡10 ጌታ የጠፉትን ሊፈልግና ሊያድን እንደመጣ ተናግሮአል።

በአዲስ ኪዳን የተገለጠው የደኅንነት መንገድ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ፈልጎን ነው የመጣው። አምላክ ሳለ ሰው በመሆን፣ ፈተናዎችን ሁሉ በማለፍ ያለኃጢአት በመሆን፣ የሰውን ኃጢአት ተሸክሞ በመስቀል ላይ በመሞት፣ ሞትንም ድል አድርጎ በመነሳት ለሚያምኑት የዘላለም ህይወት ምንጭና ወደ አብ የሚያደርሰው ብቸኛ ድልድይ ሆኗል።

ከሴቲቱም የሚወለደው ዘር የሰይጣንን ራስ እንደሚቀጠቅጥ የተሰጠው ተስፋ ቃል ከድንግል ማርያም በተወለደው በክርስቶስ ተፈጸመ። እንግዲህ ደኅንነት ወይም የዘላለም ህይወት በስራችንና በጥረታችን የምናገኘው የስራችን ፍሬ ሳይሆን እንደ ስጦታ ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ነው።

ጥያቄዎች፡

1. ከምንባቡ ክፍል በተለይም ከቁጥር 12 እንደምናገኘው የሕይወት ምንጭ ማነው? ጥቅሱን በራስህ አገላለጽ ጻፈው።

2. ሰዎች ለመዳን ከሚያደርጓቸው ነገሮች ጥቂቶቹን ዘርዝር። አንተስ ምን ታደርግ ነበር?

3. እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን ያዘጋጀው የደህንነት መንገድ ምንድን ነው?

4. እግዚአብሔር አስቀድሞ የሰጠው ተስፋ የተፈጸመው እንዴት ነው?

5. ክርስቶስ ስጋ የለበሰበት ዓላማ ምንድን ነው?

## ሠ. የሠው ድርሻ (የንባብ ክፍል ዮሐ.3)




ሰው ከኃጢአት ሊድንና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሊኖረው የሚችለው በክርስቶስ በኩል ብቻ መሆኑን ተመልክተናል። ይህ ማለት ከኃጢአት ንስሃ በመግባት በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሳዔ አምኖ ጌታን በመቀበልና ዳግመኛ በመወለድ የእግዚአብሔር ልጅ ወይም አዲስ ፍጥረት መሆን ማለት ነው። እግዚአብሔር የደኅንነት መንገድ ቢያዘጋጅም ሰው ግን ካልተቀበለው ሊድን አይችልም።

ደኅንነትን በተመለከተ የሰው ድርሻ መቀበል ብቻ ነው። ዮሐ.1፡12 ጌታን ለተቀበሉትና በስሙ ለሚያምኑት እግዚአብሔር ልጆቹ የሚሆኑበትን ስልጣን እንደሰጣቸው ይናገራል። ጌታን መቀበል ማለት እርሱን አውቆ አዳኝና ጌታ አድርጎ በግል ፈቃድ መወሰን ማለት ነው። ይህ ውሳኔ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ውሳኔ ነው። ጌታን ማወቅና መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን የደኅንነት መንገድ መረዳት ደኅንነት አስፈላጊ ነገር ነው ማለት ነው። ለምሳሌ ያልበሰለ አዕምሮ ያለው ሕጻን ጌታን ሊቀበልና ደኅንነትን ሊለማመድ አይችልም። (ዕብ.11፡6)

ደኅንነት በእምነት የምንቀበለው ስጦታ ነው። እምነት የተስፋ ማረጋገጫና የማይታይ ነገር ማስረጃ ነው። (ዕብ.11፡1) ደህንነት በአ ዕምሮአችን አውቀን የምንጨርሰው ነገር አይደለም። ያልገቡንና ተረድተን ያልጨረስናቸው ወደፊት ሙሉ በሙሉ የማንፈጽማቸው ነገሮች ይኖራሉ። ቢሆንም እምነት ማለት ባወቅነው የእግዚአብሔር ቃል መታመንና ያንንም መኖር ማለት ነው። የምናምነው እምነት ለአዕምሮአችን ለመቀበል ይከብደው ይሆናል። የእግዚአብሔር ቃል ግን እውነት ነውና፤ ሁሉ ነገራችንን ለዚያ እውነት ማስገዛት ይገባናል።

ይህ የባቡል ስዕል በደኅንነት ውስጥ የቃሉን፣ የእምነትንና የስሜቶችን ቦታና ሚና ያሳያል። የእግዚአብሔር ቃል ሁሌም ቀዳሚ መሆን አለበት። እምነታችን በእግዚአብሔር ቃል ላይ መደገፍ አለበት። ስሜቶቻችን ሁሉ ደግሞ ለእምነታችን መገዛት አለባቸው።




ይህን የስዕል ባቡር በከሰል ኃይል እንደሚንቀሳቀስ ተሽከርካሪ ብንወስደው የመጀመሪያው ክፍል የሞተሩን ቤት ነው። ሁለተኛው ደግሞ የከሰል ክፍል ሲሆን ሦስተኛው የመዝናኛ ፉርጎ ነው። የሞተሩ ቤት እስካለ ድረስ ባቡሩ መሄድ ይችላል። እንዲንቀሳቀስ ግን ከከሰሉ ፉርጎ ከሰሉን ማለትም እምነታችንን በሞተሩ ፉርጎ ማለትም በእግዚአብሔር ቃል ማድረግ ያስፈልገናል። ከሰሉን በተገቢው ቦታ ማለትም በቃሉ ላይ እንጂ ያለቦታው ማለትም በስሜታችን ላይ ማድረግ የለብንም። በተመሳሳይ ሁኔታ የፈለገው ያህል እምነት በስሜታችን ላይ ብናደርግ መንፈሳዊ ሕይወታችንን የትም አያደርሰውም።

አንዳንድ ሰዎች ማመን ስሜታዊነት ብቻ ይመስላቸዋል። ሌሎች ደግሞ በእምነት ውስት ስሜት ከቶ እንደሌለ ይቆጥራሉ። ሁለቱም ስህተት ነው። የስሜት ህልውና የማንክደው ነገር ነው። ክርስትና ስሜታዊነት ባይሆንም ስሜት የለሽነት ደግሞ አይደለም። ይሁን እንጂ ለማመን ወይም በእምነት ለማደግ በስሜቶች መደገፍ ትክክል አይደለም።

መዳን ማለት ከዘላለማዊ ሞት ወደ ዘላለማዊ ህይወት፣ ከሲያል ፍርድና ከኩነኔ ወደ ምህረትና ጽድቅ፣ ከእግዚአብሔር ጠላትነት ወደ ወዳጅነት፣ ለሰይጣን ከመገዛት የእግዚአብሔር ልጅ ወደመሆን ማለት ነው። ኢየሱስን በግል እንደ አዳኝና እንደጌታ አድርጎ በመቀበል ከ እግዚአብሔር ጋር መታረቅ ማለት ነው። “የግል” ሲባል ክርስቶስ የኔን የራሴን ኃጢአትና በደል ተሸክሞ ሞቶልኛል ማለት ነው። ኃጢአት ስንል ሁለት ዓይነት እንደሆነ ማየቱ ተገቢ ነው።  የመጀመሪያው ማንም ሰው ሲወለድ ጀምሮ ኃጢአተኛ የሆነበት ከአዳም የወረሰው መተላለፍ ነው። (መዝ.51፥5)




ሁለተኛው የግብር ወይም የድርጊት ኃጢአት የምንለው እግዚአብሔር አድርጉ የሚለንን ሳናደርግ ስንቀር ወይም አታድርጉ የሚለንን ስናደርግ ነው።  “አዳኝ” ሲባል እንግዲህ ከእነዚህ የሚያድነን መሆኑንና በኃጢአታችን ምክንያት መሞት ሲገባን በፈንታችን ሞቶ ያዳነን ወይም ደኅንነትን የሰጠን መሆኑን የሚያሳይ ነው። ኢየሱስ የሚለው ስም ትርጉም ራሱ አዳኝ ወይም መድኃኒት ማለት ነው።  “ጌታ” ስንልም አንድ ክርስቲያን ጌታን ከተቀበለ ጀምሮ ሕይወቱንና ኑሮውን የሚመራውና የሚቆጣጠረው ራሱ ሳይሆን በውስጡ ማደር በጀመረው መንፈስ ቅዱስ አማካይነት ጌታ ኢየሱስ የህይወቱ ጌታ መሆኑን ሲያሳይ ነው።

እነዚህ ሁለት ስዕሎች ራሱን የሚቆጣጠር ሰውና ጌታ የሚቆጣጠረው ሰው ምን እንደሚመስሉ ያሳዩናል። መስቀሉ የክርስቶስን ህልውና ሲያሳይ በመጀመሪይው ስዕል ውስጥ በዙፋኑ ላይ ያለው ራሱ (እ=እኔነት) ሲሆን በመስቀሉ የተመሰለው ክርስቶስ ከሰውየው ውጪ ነው።  ህይወቱም ግራ የተጋባ ነው።

በሁለተኛው ስዕል እንደሚታየው ግን የሰውየው እኔነት የንጉስነት ቦታውን ለክርስቶስ መልቀቁንና በዙፋኑ ላይ ላለው ዝቅ ብሎ እየተገዛ መሆኑን ያሳያል። ጌታን መቀበል ማለት ክርስቶስን በሚገባው ቦታ ማለትም በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ በህይወታችን፣ በኑሮአችን፣ በትዳራችንና በሌሎችም በማናቸውም መስኮች ላይ ጌታ እንዲሆን መፍቀድ ማለት ነው።

**ጥያቄዎች፡**

1. ደህንነት ማለት ምን ማለት ነው?

2. ኢየሱስን የግል አዳኝና ጌታ በማድረግ መቀበል ምን ማለት ነው?

3. ኢየሱስን ጌታው ያደረገና ያላደረገ ሰው ልዩነታቸው ምንድን ነው?

4. እግዚአብሔር ያዘጋጀውን ደኅንነት ለማግኘት ሰው ማድረግ ያለበት ምንድን ነው?

5. ደኅንነትን ለመቀበል ማወቅ ያስፈልጋል ስንል ምን ማለታችን ነው? መታወቅስ ያለበት ነገር ምንድን ነው?

6. ደህንነትን የምንቀበለው በእምነት ነው ሲባል ምን ማለት ነው?

7. ለደኅንነት ውሳኔ የፈቃድ አስፈላጊነት ምን ያህል ነው?

ደህንነትን ወይም እምነትን በስሜት ላይ ማስደገፍ የማይገባን ለምንድነው?